በአማራ ብሔራዊክልላዊመንግሥት
ፍትሕ ቢሮ
የሕግ ምክር፣ ማርቀቅና ማጠቃለል ዳይሬክቶሬት

THE AMAHARA NATIONAL REGIONAL STATE
JUSTICE BUREAU
LEGAL COUNSELING, DRAFTING AND COMPILATION
DIRECTORATE

ቁጥር፡ቁጥር፡- የሕ/ምክ/ማር/ማጠ/1458./18

ቀን፡ 13/12/2018 ዓ.ም

ለአብክመ ገንዘብ ቢሮ
ባሕር ዳር

ጉዳዩ፡ **የመመሪያ ምዝገባን ይመለከታል**

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የአስተዳደር ሥነ-ሥርዓት አዋጅ ቁጥር 292/2017 ዓ.ም መሠረት፣ ማንኛውም የአስተዳደር ተቋም አዲስ መመሪያ አውጥቶ ተግባራዊ ከማድረጉ በፊት መመሪያውን ከነማብራሪያው በመላክ፣ እንዲሁም አዋጁ ከመውጣቱ በፊት በሥራ ላይ የነበሩ መመሪያዎችን ለፍትሕ ቢሮ በመላክ እንዲመዘገብ ማድረግ እንደሚገባው ተደንግጓል።

በዚህ መሠረት የገንዘብ ቢሮ በቁጥር አብክመ/ገቢ/20 በቀን 04/12/2018 ዓ.ም በተፃፈ ደብዳቤ ከጫት ምርት ሽያጭ ላይ ቀረጥ ለመሰብሰብ የወጣ የአፈጻጸም መመሪያ 12/2014 ዓ.ም ምዝገባ እንዲከናወንለት መላኩ ይታወሳል።

ስለሆነም ፍትሕ ቢሮ በአዋጁ አንቀጽ 16 ንዑስ አንቀፅ 1 በተሰጠው ሥልጣን መሠረት የተላከለትን መመሪያ ቁጥር 12/2014 ዓ.ም በመመርመር መመሪያው በክልል ደረጃ መመሪያ ቁጥር 151/2018 ዓ.ም ሆኖ በሥራ ላይ እንዲውል የመዘገበው ስለሆነ የተመዘገበውን መመሪያ ቅጂ.05.ገጽ በዚህ ሽኚ ደብዳቤ አባሪ በማድረግ የላክን መሆኑን እንገልጻለን።

ከሰላምታ ጋር

ገረመው እሸቱ

የሕግ ምክር፣ ማርቀቅና ማጠቃለል ዳይሬክቶሬት

የክልል ዐቃቤ ሕግ

ግልባጭ//

- ለቢሮ ኃላፊ ጽሕፈት ቤት (ያለ አባሪ)
- ለፍትሓብሔርና/ሕግ ጉዳይ ዘርፍ ምክትል ቢሮ ኃላፊ ጽሕፈት ቤት
  ፍትሕ ቢሮ

Tl.No ☎ 058 222 0794/793 /058 226 52 92 ✉ 995

መመሪያ ቁጥር 151/2018 ዓ.ም

ከጫት ምርት ሽያጭ ላይ ቀረጥ ለመሰብሰብ የወጣ የአፈጻጸም መመሪያ

የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት የጫት ምርት ቀረጥን ለማስከፈል የወጣው አዋጅ ቁጥር 193/2003 ዓ.ም ከወጣ ረጅም ዓመታት ያስቆጠረ ሲሆን በዚሁ አዋጅ የጫት ምርት ማስከፈያ ታሪፍ እና ገቢው ሥለ ሚሰበሰብበት ሁኔታ መመሪያ እንደሚወጣ የተደነገገ ቢሆንም እስካሁን ድረስ ያልወጣ በመሆኑ

የህብረተሰቡን ደህንነት ለመጠበቅ እና በክልሉ ውስጥ የጫት ፍጆታ በከፍተኛ ፍጥነት እያደገ በመሄዱ ይህንን ሁኔታ ለመለወጥ የሚያግዝ የጫት ምርት ቀረጥ ክፍያ ማስቀመጥ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

በጫት ምርት ላይ የሚሰበሰበው ቀረጥ ወጥነት የሌለው በመሆኑ በቀጣይ በክልሉ በሁሉም ከተሞች እና ወረዳዎች ፍትሃዊነትን ባረጋገጠ መልኩ መፈፀም አስፈላጊ በመሆኑ፣

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ገንዘብ ቢሮ የጫት ምርት ቀረጥን ለማስከፈል የወጣ አዋጅ ቁጥር 193/2003 አንቀፅ 4(2) እና አንቀጽ 13(2) በተሠጠው ሥልጣን መሠረት ይህን መመሪያ አውጥቷል።

ክፍል አንድ

ጠቅላላ ድንጋጌ

1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "ከጫት ምርት ሽያጭ ላይ ቀረጥ ለመሰብሰብ የወጣ የአፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 151/2018 ዓ.ም" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. ትርጓሜ

በክልሉ የጫት ምርት ቀረጥን ለማስከፈል የወጣ አዋጅ ቁጥር 193/2003 ትርጉም የተሰጠው ቃል በዚህ መመሪያ ውስጥ ጥቅም ላይ የዋለ እንደሆነ ለዚህ መመሪያ አፈጻጸም የተለየ ትርጉም ካልተሰጠ በስተቀር በአዋጁ የተሰጠውን ትርጉም ይይዛል።

1/ "ቀረጥ" ማለት ከጫት ምርት መሸጫ ዋጋ ላይ ተመስርቶ የሚጣል ክፍያ ነው።

2/ "አዋጅ" ማለት የጫት ምርት ቀረጥ ማስከፈያ አዋጅ ቁጥር 193/ 2003 ዓ.ም" ነው።

3. የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ በክልሉ ውስጥ ከጫት ምርት መነሻው ተነስቶ ወደ ገበያ በሚያቀርቡ ወይም በእንስሳትም ሆነ በተሸከርካሪ ጭነው ሲያጓጉዙ በተገኙ ሰዎች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል።

ክፍል ሁለት

የጫት ምርት ቀረጥ የሚሰበሰብባቸው ቦታዎች እና ስለ ቀረጡ አሰባሰብ

4. የጫት ምርት ቀረጥ የሚሰበሰብባቸው ቦታዎች

1/ በጫት ምርት መሸጫ ላይ የሚከፈለው ቀረጥ የሚሰበሰበው ከተሞች እና ወረዳዎች የጫት ምርት ተመርቶ የሚገበያዩበትን ቦታ ለይተው ለገቢ ተቋሙ በሚያሳውቁት ቦታዎች ላይ ይሆናል።

2/ የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የጫት ምርት በይዞታው ስር አድርጎ ይዞ ሲንቀሳቀስ ወይም በእንስሳትም ሆነ በተሸከርካሪ ጭኖ ሲያጓጉዝ በተገኘበት ቦታ ላይ የጫት ቀረጥ ይሰበሰባል።

3/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 እና 2 እንደተጠበቀ ሆኖ የጫት ምርት ይዞ ሲንቀሳቀስ በአንድ ቦታ የጫት ቀረጥ በከፈለበት ቀን ድጋሚ አይሰበሰብም ወይም አይከፈልበትም።

4/ ቀረጥ ከፋዩ አንድ ጊዜ በከፈለበት ደረሰኝ በተደጋጋሚ የጫት ምርት ይዞ እንዳይንቀሳቀስ ወይም እንዳያልፍ የቀረጥ ሰብሳቢ ባለሙያዎች ደረሰኙን ሲሰጡ ምልክት ማድረግ ይኖርባቸዋል።

5/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 4 መሠረት የጫት ምርት ቀረጥ ለመክፈሉ የተሰጠውን ደረሰኝ ከተቆረጠበት ከተማ ወይም ወረዳ ውስጥ ከተቆረጠበት ጊዜ ጀምሮ ለሁለት ሰዓት ብቻ የሚያገለግል ይሆናል።

5. ስለ ቀረጥ አሰባሰብ

1/ ከጫት ምርቱ ተነስተው ለመገበያየት በተለዩት ቦታዎች ላይ ቀረጥ ይሰበሰባል።

2/ የጫት ምርት ቀረጥ በክልሉ ውስጥ ተመርቶ ከመነሻው ወረዳ ወይም ከተማ ጥቅም ላይ የሚውልና ወደ ሌላ ከተማ የሚጓጓዝ ጫት በኪሎ ግራም ብር 30 /ሠላሳ ብር/ ሂሳብ እየተሰላ ከመነሻው እንዲሰበሰብ ይደረጋል።

3/ ማናቸውም በጫት ንግድ ሥራ ላይ የተሰማራ ግብር ከፋይ በጫት ምርት ላይ ከሚከፍለው ቀረጥ በተጨማሪ በከተሞችና በመንደሮች በቀጥታ ለተጠቃሚዎች ሲሸጥ በግብር ከፋይነት በመመዝገብ የንግድ ትርፍ፣ የተጨማሪ ዕሴት ታክስ ወይም የተርን ኦቨር ታክስ የመክፈል ግዴታ አለበት።

6. ታክስ የመክፈል ግዴታ

ጫትን በይዞታው ሥር በማድረግ በማጓጓዝ ወይም በማናቸውም መንገድ ለሽያጭ የሚያቀርብ ሰው በዚህ መመሪያ አንቀፅ 5(2) ላይ የተወሰነውን ክፍያ የመክፈል ግዴታ አለበት።

ክፍል ሦስት

7. የገቢ ተቋሙ ተግባርና ኃላፊነት

ማናቸውም ወረዳና ከተማ የጫት ምርት ግብይት የሚከናወንባቸውን ቦታዎች በመለየት የመገበያያ ቦታ በማዘጋጀት ታክሱን መሰብሰብ አለባቸው።

8. ተጠያቂነት

ማናቸውም የጫት ባለ ይዞታ ወይም ባለ ንብረት የሆነ ሰው የጫት ምርት ቀረጥ ሳይከፍል ለማለፍ የሞከረ ወይም ያለፈ እንደሆነ በጫት ምርት ቀረጥ ማስከፈያ አዋጅ ቁጥር 193/2003 መሰረት ተጠያቂ ይሆናል።

9. የሪፖርት አቀራረብ

1/ ከተሞችና ወረዳዎች ከጫት ምርት ቀረጥ የተገኘውን ገቢ መጠን በመለየት ለመምሪያዎች ሪፖርት ያቀርባሉ።

2/ የዞንና የከተማ ገቢዎች መምሪያ የወረዳዎችንና የከተሞችን ሪፖርት በማጠናከር ለክልል የማሳወቅ ኃላፊነት አለባቸው።

10. የአሰራር ሥርዓት ስለመዘርጋት

ገቢዎች ቢሮ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 4 ላይ በተደነገገው መሠረት የጫት ግብይት በተዘጋጀው ቦታ ላይ እየተከናወነ ስለመሆኑ፣ እንዲሁም ታክሱ በወጣው አዋጅና በዚህ መመሪያ መሠረት ስለመሰብሰቡ ለመከታተልና ለመቆጣጠር የሚያስችል ሥርዓት ይዘረጋል።

ክፍል አራት

11. ተፈጻሚነት የሌላቸው መመሪያዎች

ከዚህ መመሪያ ጋር የሚቃረን ማናቸውም መመሪያ ወይም ሰርኩላር ወይም አሠራር በዚህ መመሪያ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖራቸውም።

12. **<u>መመሪያው ተፈጻሚ የሚሆንበት ጊዜ</u>**

1/ ይህ መመሪያ በቢሮ ኃላፊው ተፈርሞ ከወጣበት ከነሀሴ -------- ቀን 2014 ጀምሮ ተፈጻሚ ይሆናል።

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ላይ የተገለጸው ቢኖርም ይህ መመሪያ እንደገና አዲስ ቁጥር ከተሰጠበት ቀን በኋላ የሚነሳ መብት ወይም ግዴታ ሕጋዊ ውጤት የሚኖረው መመሪያው በፍትህ ቢሮ ተመዝግቦ በገንዘብ ቢሮ ድረ-ገጽ ከተጫነበት ቀን ጀምሮ ይሆናል።

ጥላሁን መሀሪ አንተነህ (ዶ/ር)

የገንዘብ ቢሮ ኃላፊ